PERMANENT MISSION OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA THE UNITED NATIONS

Date: ሐምሌ 29 ቀን 2012 ዓም
Ref. No፡ ኒዮሚ/515/2012

**በትራይ ስቴት ለምትኖሩ የሃይማኖት ተቀማት፣ የሙያ ማህበራት፣ የኮሚኒቲ አደረጃጀቶች፣**
**ለመላው ኢትዮጵያውያን፣ የንግድ ተቋማት፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ባለሃብቶች በሙሉ፣**
**<u>በያላችሁበት</u>**

**ጉዳዩ:- "<u>ወገን ለ ወገን" የድጋፍ ጥሪ</u>**

ባሁኑ ወቅት ዓለምን ከዳር እስከ ዳር ባዳረሰው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት በርካታ ሚሊዮኖችን የዚህ በሽታ ተጠቂዎች አድርጓል። ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ለህልፈተ ህይወት ዳርጓአል፣በሀገራችን ኢትዮጵያም ከፍተኛ ስጋት እየሆነ ከመጣ ወራቶች ተቆጥረዋል፤ በዚህም እስከ አሁን ድረስ በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን የበሽታው ተጠቂ ሲሆኑ በመቶዎች የሚቆጠሩ ደግሞ በዚህ ክፉ ወረርሽኝ ህይወታቸው አልፏል።

በተለይም በአገራችን የበሽታዉ ስጋትና የህሙማኑ ቁጥር ከቀን ወደቀን እየጨመረ መሄዱ አሳሳቢ ሆኗል፤መንግስት የበሽታውን ስርጭት ለመቆጣጠር የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ ነው። በርካታ የለይቶ ማቆያ ቦታዎችን አዘጋጅቷል፤ አስቸኳይ አዋጅ በማዉጣት ህዝቡ እራሱን ከበሽታው እንዲከላከል እያደረገ ነው፣የመመርመሪ ያመሳሪያዎችን በግዢም በእርዳታም እያሰባሰበ ነው፣የጤና ባለሙያዎች ቀን ከሌት በመስራት ሙያዊ ግዴታቸውን እየተወጡ ነው። ችግሩ ግን የጤና ችግር ብቻ ሳይሆን በመንግስትም በህዝቡም ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጫና አስከትሏል፣ የመንግስት ገቢ ቀንሷል፣ድሮም ከእጅ ወደ አፍ ይኖር የነበረው ህዝብ የሚበላው የእለት ምግብ የለውምና ሀገሪቱም ህዝቡም የኛን እርዳታ ይፈልጋሉ።

ይህን ችግር በመገንዘብ በሚሲዎናችን ስር ከማህበረሰቡ የተውጣጣ እርዳታ አሰባሳቢ ግብረ ሀይል ተቋቁሟል።ግብረ ሀይሉም ተከታታይ ስብሰባዎችን በማድረግ የሚከትሉትን ሃሳቦች አቅርቧል፤

- እያንዳንዱ የሃይማኖት ተቋም፣ የሙያ ማህበር፣
- የኮሚኒት አደረጃጀቶች ካላቸው ላይ የሚችሉትን የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉ፣
- እነዚሁ የሀይማኖት ተቋማትና ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ምእመናትንና የማህበር አባሎቻቸውን እርዳታ እንዲያደርጉ ጥሪ እንዲያስተላልፉ፣
- የንግድ ተቋማት፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ባለሀብቶችም እርዳታ በማድረግ ሀገራዊና ወገናዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ጥሪውን አስተለልፏል።

ለዚህም እንዲረዳ በሚሲዎኑ ስም ለዚሁ ብቻ የሚውል የባንክ ሂሳብ የተከፈተ ሲሆን ሶስት የአከፋፈል መንግዶችም ተዘጋጅተዋል፤

1. <u>በቀጥታ ባንክ ለማ ስገባት</u>:-
   Account no: 6863969850
   ABA Number: 021000089
   Bank Name: Citibank N.A.
   Payment: to combat COVID-19 in Ethiopia

2. <u>በቼክ ለመላክ</u>:-
   Payable to: Permanent Mission of the FDR of Ethiopia
   866 Second Avenue, 3rd Floor
   New York, 10017

3. <u>በክሬዲትና በዴቢት ካርድ ለመክፈል</u>
   <u>Ethiopian Covid-19</u>

ስለዘወትር ትብብራችሁ ከልብ እናመሰግናለን።

ከሰላምታ ጋር

ረዳኢ. ግርማይ
ባለሙሉ ስልጣን ሚኒስትር
በተ.መ.ድ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ቋሚ መላክተኛ ጽ/ቤት

The address to send the check is:

Permanent Mission of Ethiopia to the UN
866 2nd Avenue #3
New York, N.Y. 10017

On the memo, please put “to combat COVID-19 in Ethiopia”

---

Account title: Permanent Mission of Ethiopia to the UN
Account no: 6863969850
ABA Number: 021000089
Bank Name: Citibank N.A.
Reason of transfer payment: to combat COVID-19 in Ethiopia